# የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ ረቂቅ አዋጅ  አጭር ማብራሪያ

*መግቢያ*

በዓለም ዓቀፍ ደረጃ እ.ኤ.አ. በ2017 በተደረገ የዓለም ባንክ የዲጂታል መለያ ለልማት (ID4D) ጥናቶች መረጃ መሠረት በዓለም ዙሪያ ወደ 1.1 ቢሊዮን የሚደርሱ ሰዎች ማንነታቸውን በይፋ ማረጋገጥ አልተቻለም። በዚህም መረጃ መሰረት በዓለም ላይ ካሉ 193 የተባበሩት መንግስታት አባል የሆኑ ሉዓላዊ አገራት ውስጥ ወደ 146 ወይም 75% ከመቶ የሚያህሉ አገራት ዘመናዊና ባለብዙ ፈርጅ አገልግሎት የሚሰጥ ወጥ የሆነ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የበለጸገ የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት እንዳላቸው ከመረጃ መረቦች የተገኙ ጥናቶቸ ያሳያሉ።

ይሁን እንጂ ከላይ ከተጠቀሰው አሃዝ ውስጥ 47 ሃገራት ወይም ወደ 25% ከመቶ የሚሆኑት አገራት ዘመናዊ የዲጂታል መታወቂያ የሌላቸው ናቸው። ኢትዮጵያም ከነዚህ ሀገራት ውስጥ አንዷ ናት።

ሌሎች በዘርፉ የተደረጉ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት አንዳንድ የበለፀጉ አገራት ለምሳሌ አሜሪካ፣ ካናዳ፣ አየርላንድ፣ ወዘተ መሰረታዊ የዲጂታል መታወቂያ ባይኖራቸውም የተጠናከረና ወጥ የሆነ ዘመናዊ የሶሻል ሴኩሪቲና የክሬዲት ካርድ አሰራር በመጠቀም ዜጎቻቸው የተለያዩ አገልግሎቶችን በአስተማማኝነትና በቀላሉ ከመንግሥት የሚያገኙበትን የአሰራር ስልት ቀይሰው እየሰሩ ይገኛሉ። በአሁኑ ጊዜ ይህንን የተደራጀ የአሰራር ዘዴ በዲጂታል ቴክኖሎጂ በመታገዝ ከዲጂታል መታወቂያ ስርዓት ጋር በማቀናጀት ከነዋሪዎች የደህንነት ስጋት እንቅስቃሴ ጋር ተያይዘው ሊመጡ የሚችሉ ያልተጠበቁ አደጋዎችን ለመቀነስ የሚረዱ የተለያዩ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን የተመለከቱ የህግ ማዕቀፎችን በማውጣት ላይ እንደሆኑ ለመገንዘብ ይቻላል።

በኢትዮጵያ የዜጎች መታወቂያ አሰጣጥ ስርዓት ታሪካዊ ዳራ የሚያሳየው፤ ከጣልያን ወረራ በኋላ ከ1934 ዓ.ም. ጀምሮ ደረጃቸውን ያልጠበቁ፣ ወጥነት የሌላቸው መታወቂያዎች በከተማና በገጠር የአስተዳደር እርከኖች ሲሰጡ እንደነበር መረጃዎች ያመላክታሉ። በሌላ በኩል ነዋሪዎች የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ መንጃ ፍቃድን፣ የተማሪ እና የመሥሪያ ቤት መታወቂያዎችን ለመታወቂያነት ይዘው እንደሚንቀሳቀሱና እንደሚገለገሉ ይታወቃል። እነዚህ የመታወቂያ ካርዶች የነዋሪዎችን ማንነት ለማረጋገጥ እንጂ አስተማማኝ የመለያ ሰነድ ሆነው ሊያገለግሉ ባለመቻላቸው ሰነዶችን በማረጋገጫነት በመጠቀም አገልግሎት የሚሰጡ የመንግሥት ተቋማት ለተለያየ የማጭበርበር ድርጊት ሰለባ እንደሆኑ በባንክና በፖሊስ ተቋማት የተገኙ መረጃዎች ያረጋግጣሉ።

የኢፌዲሪ መንግስት የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት በአግባቡ በሃገሪቱ ቢዘረጋ ሊያስገኝ የሚችለውን ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እድገቶች ከግምት በማስገባት ከላይ የተመለከቱትን ከዲጂታል መታወቂያ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የስርዓትና የአደረጃጀት ችግሮችን ለመፍታት ባስቀመጠው ጠንካራ ትኩረት በጠቅላይ

ሚኒስትር ጽ/ቤት ስር ልዩ ፕሮግራም ቢሮ በማደራጀት በዘርፉ ስራው እየተሰራ ሲሆን፣ ስራውን ውጤታማ ለማድረግ ከሚጠቅሙ ጉዳዮች አንዱ የሕግ ማዕቀፍ ነው። ስለሆነም ሕገ-መንግስቱን ያከበረ፣ ዘመኑን የሚመጥን እና ከዲጂታል መታወቂያ ፅንሰ-ሀሳብ ጋር የተጣጣመ አዋጅ የተዘጋጀ ሲሆን፣ የአዋጁ ማብራሪያ በሚከተለው መልኩ ቀርቧል።

## 1. የአዋጁ አስፈላጊነት

የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ማለት በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ ግለሰቦች መሰረታዊ የሆኑ የግል ዲሞግራፊክ እና ተፈጥሮአዊ የሆነውን የአይን፣ የጣትና የፊት የባዮሜትሪክ መረጃዎችን መዝግቦ በማዕከላዊ ቋት መያዝ ሲሆን፤ ማንኛውም ነዋሪ የዲጂታል መታወቂያ ምዝገባ ካከከናወነ በኋላ ልዩ ቁጥር በመሥጠት የተደራጀ እና አስተማማኝ የዲጂታል መታወቂያ የሚሰጥበት ሥርዓት ነው። በሀገራችን አስተማማኝ የዲጂታል የመታወቂያ ሥርዓት መዘርጋት፣ ዜጎች እና በሃገሪቱ ውስጥ በህጋዊ መንገድ የሚገኙ ነዋሪዎች የመታወቅ መብታቸውን ከማረጋገጥ ባለፈ በመንግስት እና በግሉ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች ውስጥ በሚንቀሳቀሱ የአገልግሎት ሰጪና ተጠቃሚ አካላት መካከል በሚኖር ግንኙነት ላይ ከፍተኛ እምነት እንዲዳብር ያደርጋል። ከዚህ በተጨማሪ ለዜጋው በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ የግልጽነትና የተጠያቂነት አሰራር ሥርዓትን እንዲዘርጋና የተሳለጠ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት እንዲኖር አመች ሁኔታዎችን ይፈጠራል። ሌላውና ዋነኛ የዲጂታል መታወቂያ ጠቀሜታ ዜጎችን በግልጽ መታወቅ በማስቻሉ ለሃገሪቱ ህዝቦች ሰላምና ደህነነት መጠበቅ ጉልህ አስተዋጻኦ ያደርጋል።

የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ከላይ የተመለከቱት ጠቀሜታዎች ያሉት ቢሆንም በተጨባጭ ግን በሀገራችን በሃገር አቀፍ ደረጃ የሚያገለግል ወጥ፣ አስተማማኝና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደራጀ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት የለም። ይህም በመሆኑ ዜጎችን ከሌሎች ግለሰቦች በልዩ ሁኔታ ለመለየት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አልተቻለም ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት አሰጣጥ ሂደቶች የተሳለጡ እንዳይሆኑ አድርጓ፣ አንድ ሰው በተለያየ ስም እና ማንነት በርካታ መታወቂያዎችን በመያዝ የተለያየ የወንጀል ድርጊቶች እንዲሳተፍ እድል ፈጥሯል። ከዚህም በተጨማሪ በአግባቡ ሊዘጋጁና ሊተገበሩ የሚገባቸው የህዝብ ብዛትና ምጣኔ ሃብታዊ፣ እንዲሁም ወሣኝ የማህበራዊ የልማት መለኪያዎች አግባብነት ያለውን አሠራር በመከተል ለመሰብሰብ እና ለማጠናቀር ያልተቻለ ሲሆን በዚህም ምክንያት ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ኘሮግራሞችን ለመቅረፅ እና ለመተግበር የሚያስችሉ መረጃዎችን ማግኘት አልተቻለም።

በመሆኑም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የበለፀገ፣ ዘርፍ ተሻጋሪ፣ መሰረታዊ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት በመዘርጋት፤ ሃገራዊ ሰላምና ድህንነትን ለማጠናከር፣ ሃገራዊ ልማትን በአግባቡ ለማቀድ፤ ምጣኔ ሃብታዊ ሽግግር ለመፍጠር፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ ፖሊሲዎች ሲቀረጹና ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ የልማት ሥራዎች ሲከወኑ

ድግግሞሽን እና አካታች ያለመሆን ችግርን በቀላሉ በመለየትና በመቅረፍ የሀብት ብክነትን በመቀነስ በነዋሪዎች መካከል ፍትሀዊነትን ለማስፈን እና ከወንጀል ጋር የተያያዙ ስጋቶችን በመቀነስ ሃገራዊ ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት የአዋጁን መውጣት አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡

## 2. የህጉ የማርቀቅ ሂደት

በሃገሪቱ የዲጂታል መታወቂያ አስፈላጊነትና በቀድሞ የብሔራዊ መታወቂያ አዋጅ አተገባበር ላይ በአለም ባንክ እ.ኤ.አ በ2019 የተደረገው ሁሉን አቀፍ ጥናትና እንዲሁም በዲጂታል መታወቂያ ፕሮግራም በ2022 የተደረገው የሁኔታ ትነተና የጥናት ሰነድ ግኝቶች እንደሚያመለክቱት በሃገሪቱ የዲጂታል መታወቂያ አለመዘርጋቱ ዘርፈ ብዙ የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊ እና የፖለቲካዊ ጉዳቶች ያስከተለ በመሆኑ የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት አግባብ ባለው የህግ ማእቀፍ ተደግፎ በተደራጀ መንገድ መዘርጋት እንዳለበት አመልክተዋል፡፡ ከላይ የተመለከቱት ሁለት ጥናቶች ከተጠኑ በኋላ ጥናቶቹን መሰረት በማድረግ ረቂቅ አዋጁ የተዘጋጀ ሲሆን በረቂቁ ላይ አምስት ጊዜ የፌዴራልና የክልል የሚመለከታቸውን አካላት ያሳተፈ ግብአት ማሰባሰቢ ውይይት ተካሂዷል፡፡ በውይይቶቹ የተገኙ ግብአቶችን ወደ ረቂቁ ለማካተትም ተሞክሯል፡፡ በግብአቶቹ መሰረት የመጨረሻው ረቂቅ ከተዘጋጀ በኋላ ረቂቁን ለፍትህ ሚኒስቴር ሁለት ጊዜ በመላክ አስተያየት እንዲሰጥበት የተደረገ ሲሆን፣ ፍትህ ሚኒስቴር በሰጠው አስተያየት ተስተካክሏል፡፡ እንዲሁም የፍትህ ሚኒስቴር ባለሙያዎች በአካል በመምጣት እንዲያግዙን ተደርጓል፡፡

## 3. የአዋጁ አደረጃጀት

አዋጁ በአምስት ክፍሎች የተደራጀ ሲሆን፤ በክፍል አንድ ጠቅላላ ድንጋጌዎች የተካተቱ ሲሆን አጭር ርዕስ፣ ትርጓሜ፣ የተፈጻሚነት ወሰን እና የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ ተቋምን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን አካቷል፡፡ በክፍል ሁለት ስለ ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት ዋና ዋና መርሆዎች ፣ ምዝገባ እና አገልግሎት አሰጣጥን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ማለትም ስለ መርሆዎች፣ ስለ ምዝገባ ስርዓት፣ ስለ የግል መረጃ፣ ህፃናት መታወቂያ ስለሚያገኙበት ሁኔታ፣ ስለ ልዩ ቁጥር፣ ስለ ዲጂታል መታወቂያ ካርድ፣ ስለ ቋንቋ እና የዲጂታል መታወቂያ መረጃ ልውውጥን የመመለከቱ ድንጋጌዎች ተካተውበታል፡፡ ክፍል ሶስት ስለ ተጠቃሚ አካላት እና ስለ ማረገገጥ አካላት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡ ክፍል አራት ስለ የግል መረጃ፣ ስለ መረጃ መጭበርበር ወይም መሰሳት፣ ስለለ ግለሰብ መረጃ አያያዝና ደህንነት፣ ስለ ተመዝጋቢ መረጃ ጥበቃ እና ስለ ቅሬታ አራረብና አፈታት ስርዓት የሚመለከቱ ድንጋዎች ተካተዋል፡፡በክፍል አምስት ስለመተባበር ግዴታ፣ ስለተሻሩ ህጎች፣ እና መሰል ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡

## 4. የአዋጁ ይዘት

*የአዋጁ ይዘት  የባዮሜትሪክና የዲሞግራፊክ ዳታን በመሰበሰብ የዲጂታል መለያ ልዩ ቁጥር ያለው እንዲሆን ተደርጎ የሚዘረጋን ሥርዓት የሚፈጥር አዋጅ ነው።*

*የዲጂታል መታወቂያ አዋጅ ተፈጻሚነት በኢትየጵያ ውስጥ በሚገኝ በማንኛውም ሰው ላይ  ሲሆን በዲጂታል መታወቂያ አዋጅ ሥርዓት የሚሰበሰቡት መረጃዎች በቀጥታ ከእያንዳንዱ ዜጋ እና ህጋዊ ነዋሪ (የውጭ ሃገር ዜጎችንም ጨምሮ) ነው። በዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት የሚመዘገብ ነዋሪ መረጃውን በተፈለገው ዓይነትና ቅርጽ ለመስጠት ውዴታውንና ፈቃዱን መግለጽ አለበት።  የዲጂታል መታወቂያ አዋጅ ዋንኛ ትኩረት የዜጎችን የዴሞግራፊክና የባዮሜትሪክና መረጃዎች በመመዝገብ፣ በማከማቸትና እንደአስፈላጊነቱ የዜጎችን ማንነት ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ በማዋል እንዲሁም የመረጃዎችን ደህንነትና ትክክለኛነት በማረጋገጥ ማከማቸት ላይ የተመሠረተ ነው። ስለሆነም ለዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚሰበሰቡ መረጃዎች የሚሰበሰቡት የዜጐችን ማንነት ለመለየት፤ለዜጐች ቀልጣፋና አስተማማኝ አገልግሎቶች ለመስጠት የሚያስችል ሥርዓትን ለመዘርጋት፤የኅብረተሰቡንና ደህንነት ለማረጋገጥ፤ ተጠያቂነትና ግልጽነት ለመፍጠርና የስታትስቲክስ መረጃ ምንጭ የሆኑ ሥርዓቶችን ለመገንባት ነው። ዲጂታል መታወቂያ መረጃ የመሰብሰብ ሥራ ተከታታይነትና ቀጣይነት ያለው ነው። ለዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ትክክለኛና ያልተደጋገሙ መሆን ይኖርባቸዋል። አግባብነት ያለው ዲጂታል መታወቂያ ተቋም ይህንኑ የማረጋገጥ ግዴታም አለበት። ለዚህም የሚረዳ የቴክኖሎጂ ማእቀፍና ሃገራዊ የመረጃ ቋት ይገነባል።*

*በኢትዮጵያ የሚዘረጋው የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት መዘርጋት መሰረታዊ  ዓላማዎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያውና ዋንኛው ሁሉን አቀፍ፣ ወጥና አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ፣ ነዋሪዎች የሚመዘገቡበትን ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት በመዘርጋት የተመዝጋቢዎችን መረጃዎች በመያዝ የዲጂታል መታወቂያ አጠቃቀም ስርዓትን ሕጋዊ መሠረት እንዲኖረው ማድረግ ሲሆን ሁለተኛው በተጠቃሚ አካላት በአገልግሎት ሰጪና ተመዝጋቢ መካከል የሚኖር ግንኙነት እና መስተጋብር በእምነት ላይ የተመሠረተ ማዕቀፍን መዘርጋት ነው። ሶስተኛውና የመጨረሻው ዓላማ የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እድገትና ተገማችነትን በማረጋገጥ ተጠያቂነትን፤ ግልፅነትን እና የነዋሪዎችን ሁለንተናዊ ደህንነት ማረጋገጥ፤*

*ለዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚሰበሰቡት መረጃዎችም በአግባቡ የተጠበቁ በተጨማሪም የዜጐችን እውነተኛ ማንነት በተደራጀ መንገድ ለመለየት የሚያስችል ደረጃውን የጠበቀና ምስጢራዊ መለያ ያለው በቀላሉ የማይበላሽና የማይለወጥ የዲጂታል መታወቂያ ለመስጠትና አግለገሎት ሰጪ ተጠቃሚ አካላት ባለጉዳዮቻቸውን በአስተማማኝ መንገድ ለማረጋገጥ የሚውሉ መሆን አለባቸው።*

*የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የተለያዩ  መርህዎች ያሉት ሲሆን፡  ዋና ዋና መርህዎቹም ሁሉን አቀፍ፣ ከአድሏዊ አሠራር ነፃ የሆነ ተደራሽ እና ለአጠቃቀም ምቹ፣ አመኔታ የሚጣልበት እና ህጋዊ መሠረት ያለው መለያ ወይም የመታወቂያ ማረጋገጫ ሥርዓት መዘርጋት ናቸው። በተጨማሪም የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት*

አዋጅ የሃገራችንን የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎችን መረጃና ደህንነት፥ እንዲሁም ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እና ተደራሽነትን ለማስፋት መሠረት ሆኖ እንዲያገለግል ታስቦ የተረቀቀ አዋጅ ነው። ዲጂታል መታወቂያ አዋጅ ከሥርዓቱ ንድፍ ጀምሮ ግላዊነት እና ደህንነቱ የተጠበቀ ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ ፤ ሴክተር እና ድንበር ተሻጋሪ ሆኖ ከሌሎች ሥርዓቶች ጋር መናበብ የሚችል ፤ የቴክኖሎጂ አቅርቦት ሉአላዊነትን የሚያረጋግጥ እንዲሁም ዘላቂ የፋይናንስ እና የክወና ዕቅድ ያለው ስረዓት ነው።

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ አዋጅ ቁልፍ መርህ የሚሰበሰቡ መረጃዎች የተመጠነ የመረጃ አሰባሰብ መርህንና የተሰበሰበው መረጃ ለታለመለት ዓላማ ብቻ መጠቀም መርህን/data minimization and use it for intended purpose only principle/ የሚከተል ነው። የተመጠነ የመረጃ አሰባሰብ መርህ ማለት ለዲጂታል መታወቂያ የሚሰበሰቡ መረጃዎች የዲጂታል መታወቂያ ዓላማን ለመፈጸም የሚያስፈልገውን አነስተኛውን የግል መረጃ መጠን መለየት፣ መያዝና መሰብሰብ አለበት ግን ከዚያ በላይ መሰብሰብ አይቻልም። የተመጠነ የመረጃ አሰባሰብ መርህን የግል መረጃን የሚሰበሰበው በቂ፣ ተዛማጅ እና ለተፈለገው ዓላማ በቻ በተገናኘ አስፈላጊ ለሆኑ ነገሮች ብቻ የተገደበ መሆን አለበት የሚል መርህ ነው። በሌላ በኩል የተሰበሰበውን መረጃ መጠቀም የሚቻለው ለታለመለት ዓላማ ብቻ ነው።የሚለው መረጃ የዲጂታል መታወቂያ ስርዓቱ የግል መረጃ ደህንነት እና ጥበቃ የተረጋገጠበት ፤ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓቱን የሳይበር ደህንነት እና የማህበረሰቡን የዲጂታል መታወቂያ መብቶች የሚያስጠብቅ የህግ ማዕቀፍ የተዘጋጀለት ፤ ግልፅ ተቋማዊ ሃላፊነቶችና የተጠያቂነት ማዕቀፎች ያሉት ፤ እንዲሁም የነዋሪዎችን ቅሬታ የሚፈታበት አስተማማኝና ገለልተኛ የቅሬታ አፈታት ሥርዓት ያለው መሆን አለበት፤ተጠቃሚ አካላትም የነዋሪ ማንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የዲጂታል መለያ ስርዓትን በሚዘረጉበት ጊዜ ከዲጂታል መታወቂያ የቴክኖሎጂ ስርዓት እና ከህግ ማዕቀፉ ጋር በተጣጣመ መልኩ መተግበር እንደሚኖርበት ያስቀምጣል፤

በተጨማሪም የዲጂታል መታወቂያ አገልግሎት ያለ ልዩነት ለሁሉም ሰው ተደራሽ ከማድረግ አንጻር መረጃዎችን አሟልቶ ለተመዘገበ ማንኛውም ተመዝጋቢ የዲጂታል መታወቂያ ልዩ ቁጥር የሚሰጥ ነው። እንዲሁም የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሌሎች ማናቸውም የነዋሪ መለያ መረጋገጥ ለሚጠይቁ ተግባራት ማረጋገጫ ምንጭ ሆኖ እንዲያገለግል በሚያስችል አግባብ የሚደራጅ ስርዓት ነው። ስልሆነም በሀገሪቱ የሚገኙ ተጠቃሚ አካላት፣ የነዋሪ ማንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የባዮሜትሪክ እና የዲጂታል መለያ ስርዓትን በሚዘረጉበት ጊዜ ከዲጂታል መታወቂያ የቴክኖሎጂ ስርዓት ጋር በተጣጣመ መልኩ መተግበር እንዳለባቸው ህጉ ይደነግጋል።

በሌላ በኩል በመንግስት ለሚሰጡ የነዋሪነት መታወቂያ፥ የወሳኝ ኩነት መረጃዎች እና ሌሎች የግለሰብ ልዩ መታወቂያ አገልግሎቶች መሠረት በመሆን የሚያግልግል ሆኖ የሚድራጅ ሲሆን፣ በቀጣይ ለመንግስት አመራር ውሳኔ ለመስጠት በሚያመች መልኩ የዴሞግራፊክ ስርዓት በመዘርጋት ልዩ ልዩ የዜጎችንና በሀገሪቱ ነዋሪ የሆኑ ግለሰቦችን መረጃ አደራጅቶ ለመያዝ በሚያስችል መልኩ ይቋቋማል።

ባጠቃላይ በዚህ ህግ መሰረት የመሠረታዊ መታወቂያ አገልግሎትን ለመስጠት የሚሰበሰቡ የባዮሜትሪክ መረጃዎችን የመሰብሰብ ሥልጣን የዲጂታል መታወቂያ ተቋም ወይም ተቋሙ የፈቀደለት አካል ብቻ ስልመሆኑ አዋጁ ይደነግጋል። የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ መረጃ ቋዋት ሀገራዊ ደህንነቱና ሉዐላዊነቱ በተጠበቀ ለመንግስት እና ለአመራር ውሳኔ ለመስጠት በሚያመች መልኩ የዴሞግራፊክ ስርዓት በመዘርጋት  ልዩ ልዩ የዜጎችንና በሀገሪቱ ነዋሪ የሆኑ ግለሰቦችን መረጃ አደራጅቶ ለመያዝ በሚያስችል መልኩ ይቋቋማል።

ወደ ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚገቡ የግል መረጃዎች ከላይ በተገለጸው የተመጠነ የመረጃ አሰባሰብ መርህ መሰረት የእያንዳንዱን ተመዝጋቢ የዲሞግራፊክ መረጃ እና ባዮሜትሪክ መረጃን ያካተተ መሆን  እንዳለበት ህጉ ያስቀምጣል። በዚህመ መሰረት የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚያካትታቸው መረጃዎች አራት ብቻ ሲሆኑ አእነዚህም፡ ሙሉ ስም  (የአባት ስም የአያት ስም ፤ ወይም በዚህ መልክ የተደራጀ ህጋዊ ስም ለሌለው ተመዝጋቢ ተቋሙ ህጋዊ የሆነውን ስያሜ)፣  የትውልድ ቀን፣ ወር እና ዓመት ፤ ፆታ እንዲሁም የመኖሪያ አድራሻ ናቸው። ሆኖም የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት  ዜግነት ፤ ስልክ ቁጥር፤ የኢሜይል አድራሻ፤ ፖስታ አድራሻ፤ አእና ሌሎች ጥንቃቄ የማይፈልጉ መረጃዎች  በአማራጭነት ሊይዝ አእንደሚችል ይደነግጋል።

ቋንቋን በተመለከተ በዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚመዘገቡ መረጃዎች የአገሪቱን ህገ መንግስት መሠረት ያደረገ መሆን እንዳለበትና በፌዴራል የሥራ ቋንቋ እና ምዝገባው በሚካሄድበት ክልል የስራ ቋንቋ እንደሚከናወን በህጉ የተመለከተ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ በእንግሊዘኛ ቋንቋንም ሊያካትት እንደሚችል ተመልክቷል። የኢንግሊዘኛ ቋንቋን መጠቀም ያስፈለገበት ዋንኛ ምክንያት በዲጂታል መታወቂያ ስርዓት በዋንኛነት ዘመናዊ ቴክኖሎጂን የሚጠቀምና አለማቀፋዊ መጣጣም አእንዲኖረውና ተግባቦት እንዲፈጥር ታስቦ ነው።

የዲጂታል መታወቂያ ተቋም በመረጃ ቋቱ የሰበሰባቸውን መረጃዎች በጥብቅ ደህንነት እንዲያስቀምጥ እና ያለ ግልሰቡ ፈቃደኝነት ለሌላ ለማንኛወም ሶሰተኛ ወገን እንዳይለዋወጥ የሚያስገድድ አሰራር በሕጉ ተደንግጓል። ሁለቱ ተቋማት የመረጃ ሥርዓታቸውን ተመጋጋቢ በሆነ መልኩ ማደራጀት ይኖርባቸዋል። ይህም መረጃ በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመጠቀም ረገድ ወጥ የዲጂታል  አሰራሮችን መቅረጽ እንደሚኖርባቸው ለማመልከት ነው። ዲጂታል መታወቂያ ጉዳዮች የተሰበሰቡትን መረጃዎች ዜጎችን ለሚጎዱ ተግባራት እንዳይውሉ ተቋማቱ በከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲይዟቸው በሕጉ ግዴታ ጥሏል።

በተመሳሳይ መልኩ መረጃውን የሚሰጡ ዜጐች የሚያቀርቡትና የሚያስመዘግቡት መረጃ ትክክለኛና ያልተጭበረበረ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው። መረጃዎች የሚሰበሰብበት ሥርዓትም ሆነ የሚመዘገቡ መረጃዎች ከስህተትና ከድግግሞሽ የፀዱ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ መሆን ይኖርበታል።

ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት ጉዳዮች የተሰበሰቡ መረጃዎች በአግባቡ መከማቸትና ደህንነታቸውና ምስጢርነታቸውን መጠበቅ እንዳለበት ህጉ ይደነግጋል። ማንኛውም የተሰበሰበ መረጃ  በቀላሉ እንዳይለወጥ፣

እንዳይሰረዝ፣ እንዳይበላሽ ወይም ከተፈቀደላቸው ሰዎች  ውጪ በሌላ አካል እጅ እንዳይገባ ብርቱ ጥንቃቄ መደረግና ጠንካራ የመረጃ ደህንነት ሥርዓት መዘርጋት እንዳለበት ህጉ ያስገነዝባል።

ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት ተቋም ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ተጠቃሚ ተቋማት ጋር የመረጃ ልውውጥ የሚያደርጉበትም በጥብቅ የግል መረጃ ደህንነት ጥበቃ ማእቀፍ ይተገበራል። በዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የተሰበሰቡ መረጃዎች ለሌላ አካል ተላልፈው የሚሰጡት በሕግ የተመዘገቢወን የግል መረጃ ጥበቃ ማእቅፍ ሳይጥስ ወይም በግለሰቡ ፈቃድ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲሆን የሚያስገድድ ሥርዓት እንደሚኖር በረቂቁ ህጉ ተመልክቷል።

በአዋጁ ላይ የቀረበው ሌላኛው ጉዳይ ስለ ዲጂታል መታወቂያ ካርድ ነው። እያንዳንዱ ዲጂታል መታወቂያ ተመዘጋቢ የሆነ ሰው ዲጂታል መታወቂያ ካርድ ይዘጋጃል። ማንኛውም ዲጂታል መታወቂያ ካርድ በአማርኛ በእንግሊዘኛ እና የምዝገባ ጽሕፈት ቤቱ በሚከናወንበት ብሔራዊ ክልል የሥራ ቋንቋ የተለየ ከሆነ በክልሉ የስራ ቋንቋ ይዘጋጃል። ይህም ዲጂታል መታወቂያ ካርድ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት እንዲኖረው፣ ብሔራዊ ክልላትም ለሚሰጡት አገልግሎት አመቺ እንዲሆን እና ዜጎች ለትርጉም ተጨማሪ ወጪን እንዳያወጡ የሚረዳ ነው። ከዚህ በተጨማሪ እንደ ሀገር ወጥ የሆነ ሥርዓትን ለመዘርጋት ጠቃሚ አሠራር ይሆናል።

የተለያዩ ሀገራት የዲጂታል መታወቂያን የአገልግሎት ዘመን እንደነባራዊ ሁኔታቸው ከአምስት እስከ አስር ዓመት ድረስ ይደነግጋሉ።

በርካታ የበለጸጉ ሀገራት ዲጂታል መታወቂያ መስጠትን እና ማሳደስን እንደ አንድ የመንግስት የገቢ ምንጭ በመውሰድ ዜጎቻቸው ለዲጂታል መታወቂያ አገልግሎት ከፍ ያለ ገንዘብ እንዲከፍሉ የሚያደርግ ሥርዓት ዘርግተዋል። በኢትዮጵያ ዜጎች ከሚገኙበት የኢኮኖሚ ደረጃ ይህን መሰል ሥርዓት መዘርጋት አስቸጋሪ ይሆናል።

የዚህ ሕግ አፈጻጸም ውጤታማ እንዲሆን ሁሉም ሰው የመተባበር ግዴታ ተጥሎበታል።

## ማጠቃለያ

በአጠቃላይ ይህ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ህግ፣ ቀድሞ በብሔራዊ መታወቂያ ስርዓት ላይ የነበሩ ላለፉት አስር አመታት አላሰራ ያሉ ጉድለቶችን አርሞ ፤ የተደጋገሙ ስርዓቶችና የስራ ድግሞሞሽ (duplication of effort) እንዳይፈጠሩ በሚያስችል መልኩ በሃገሪቱ ጠንካራ፣ ውጤታማና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደራጀ ፤ የሁሉንም የአገሪቱ ነዋሪዎች በአስተማማኝ መንገድ ለመለየት የታቀደ ሥርዓት ነው።